በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰበር መ/ቁ/206996

ህዳር 30 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ ቢዲኤፍሲ ኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ድርጅት ኃ/የተ/የግ/ማህበር -ምንታይ መኮንን ቀርበዋል

ተጠሪ፡ አቶ በላቸው ጉተማ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ የሰራተኛ ደመወዝ ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነዉ፡፡ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን ጅማ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን የአሁኑ አመልካች ላይ ባቀረበው ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በቀን 01/07/2000 ዓ.ም ተቀጥሮ በ5000 ሄክታር መሬት ላይ የሚለማ የቡና እርሻ ስራ አስኪያጅ፣ በአሁኑ ሰዓት ደግሞ የድርጅቱ አማካሪ በመሆን እየሰራሁ እያለ በአሁኑ ሰዓት በኮቪድ በሽታ ምክንያት በችግር ውስጥ መሆኔ እየታወቀ እኔ እስከአሁን መስሪያ ቤት ተገኝቼ ስራ እየሰራሁ እያለ ከታህሳስ ወር 2012 ዓ.ም ጀምሮ ደመወዝ እየተከፈኝ ስላልሆነ የወር ደመወዝ ብር 10,000.00 ጥቅማ ጥቅም ብር 1,500 እስከ ግንቦት ወር 2012 ዓ.ም ያልተከፈለኝ ብር 69,000 የጠበቃ አበል ብር 15% እና ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡አመልካች ባቀረበው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

መልስ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል በደብዳቤ ቁ. ቢዲኤፍሲ/0034/2012 በቀን 28/03/2012 ዓ.ም ተቋርጧል፣ ተጠሪ ስራ አስኪያጅ ሆኖ እያለ የተጠራቀመ ደመወዝ ጥያቄ ህጋዊነት የለውም፣ውሉ ተቋርጧል እንጂ ባይቋረጥ እንኳን ላልተሰራ ስራ የሚከፈል ደመወዝ የለም፣ተጠሪ ያለማው 352 ሄክታር መሬት ብቻ ነው፣ የተጠሪ ክስ ውድቅ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የወረዳዉ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ የአመልካች ምስክሮች የስራ ስንብት ደብዳቤ ለተጠሪ ስለመድረሱ ወይም አለመድረሱ እንደማያውቁና በምስክርነት ሲመጡ በጠበቃ እጅ ያዩ መሆኑን የመሰከሩ በመሆኑ ውሉ መቋረጡና ተጠሪን መድረሱ ሳይረጋገጥ ውሉ ተቋርጧል ማለት አይቻልም፣የተጠሪ ምስክሮ ተጠሪ ጅማ ጽ/ቤት ተመድቦ እየሰራ መሆኑ ሲገልጹ የአመልካች ምስክሮች ግን በጅማ ከተማ ከተዛወሩ በኋላ ስራ ላይ መሆናቸው አለመሆናቸው ያላወቁ ስለሆነ ተጠሪ ስራ ላይ የሉም ማለት አይቻልም በማለት ከህዳር 2012 ዓ.ም እስከ ግንቦት 2012 ዓ.ም ያለውን የ6ወር ደመወዝ ብር 69,000 እና 15% የጠበቃ አበል 1000 ወጪና ኪሳራ ጋር ለተጠሪ እንዲከፈል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት የግራ ቀኝ ክርክር ከስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጋር መርምሮ ተጠሪ ከስራ ስለመሰናበቱ በማስረጃ ስላልተረጋጠ ተጠሪ የአመልካች ቋሚ ሰራተኛ ነው፤ ተጠሪ ከህዳር ወር 2012 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ ስለመቆየቱ የተጠሪ ምስክሮች እራሱ ተጠሪ ስራ ላይ እንደነበረ የነገራቸው መሆኑ እንጂ እራሳቸው እንዳማያውቁ፣እንዲሁም የአመልካች ምስክሮች ቃል ተጠሪ ከህዳር ወር ጀምሮ ስራ ላይ እንዳልነበረ ያስረዳል፣ ስለዚህ ተጠሪ ከህዳር ወር 2012 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ይገባ እንደነበር እስካልተረጋገጠ ድረስ ላልሰራ ስራ የደመወዝ ክፍያ መጠየቁ የህግ መሰረት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር አመልካች ለመክፈል አይገደድም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መዝገቡን መርምሮ ተጠሪ በህጉ መሰረት ከስራ የተሰናበቱ እና ስራ ላይ ያልነበሩ መሆኑ አመልካች በማስረጃ ለማረጋገጥ አሰሪ የህግ አስገዳጅነት ያለው ቢሆንም ይህንን ግዴታ አመልካች ያልተወጣ መሆኑ፣ከፍተኛ ፍ/ቤት ባንድ በኩል በህጉ መሰረት ከስራ አላተሰናበተም በሌላ በኩል ስራ ላይ መሆኑ አልተረጋገጠም ሳይሰራ ደመወዝ አይከፈልም በማለት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉ የህግ አካሄድ የጠበቀ አይደለም፣ስለዚህ ተጠሪ በህጉ መሰረት ከስራ የተሰናበተ መሆኑን እና ከታህሳስ ወር

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

2012 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት ወር 2012 ዓ.ም ስራ ላይ ያልነበረ መሆኑን አመልካች በማስረጃ ሳያረጋግጥ ጥያቄው ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ በመሻር የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡ተጠሪ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ በኋላ ደግሞ የድርጅቱ ከፍተኛ አማካሪ በመሆን በማገልገል ላይ እያለ የስራ ውሉ በ28/03/2012 ዓ.ም ተቋርጧል፣ተጠሪ የስራ መሪ ነው በማለት በስር ፍ/ቤት እየተከራከርን እንዲሁም አመልካች የፌዴራል ተመዝጋቢ ድርጅት ስለሆነ የወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም በማለት እየተቃወምን ያለምንም በቂ ምክንያት ክርክሩን አልፈው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ እንዲዳኝ መደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት በመሆኑ እንዲሻርልን፤ የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በ28/03/2012 ዓ.ም ሲሆን ተጠሪ ክስ ያቀረበው በ08/11/2012 ዓ.ም በመሆኑ 6 ወር ካለፈ በኋላ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል የሚለው ክርክር መታለፉ ስህተት ነው፤ የስራ ውል ስለመቋረጡና ደብዳቤውም በወ/ሮ ደራርቱ በላይ አማካኝነት በእጃቸው ተሰጥቷቸው ካነበቡ በኋላ አልቀበልም በማለት መልሰው እያለ ይህም በስር ፍ/ቤት በምስክሮች ተረጋግጦ እያለ የስራ ውሉ መቋረጡ አልተጋገጠም በማለት የተሰጠ ውሳኔ ስህተት ነው፤የተጠሪ የስራ ውል ከተቋጠ በኋላ ተጠሪ ስራ ሰርቶ እንደማያውቁ በምስክሮች ተረጋግጦ እያለ ያልተሰራ ስራ ደመወዝ እንዲከፈል መወሰኑ ስህተት በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እና የወረዳ ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሮ የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲፀናልን በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ድርጅቱ በፌዴራል ተመዝጋቢ ከመሆኑ አንፃር ወረዳ ፍ/ቤት አከራክሮ የወሰነበት አግባብ እንዲሁም ተጠሪ ሥራ አስኪያጅ ነው ተብሎ ባለበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤት ይህንን አልፎ ሰራተኛ ነው ተብሎ የተወሰነበት አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ በቀን 01/10/2013ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልስ ተጠሪ የስራ መሪ ሳይሆን ከ2000 ዓ.ም እስከ ግንቦት 30/2011 ዓ.ም የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ መሆኑ የሚካድ አይደለም፣ ነገር ግን በቀን 01/10/2011 ዓ.ም በደብዳቤ BDFC/0024/2011 ድርጅቱ በፃፈው ደብዳቤ የስራ አስኪያጅነት ስራ መስራት ባለመቻሌ ከሰኔ 1/2011 ዓ.ም ጀምሮ በጅማ ከተማ ባለው የድርጅቱ ጽ/ቤት የነበረው ደመወዝ እየተከፈለኝ የድርጅቱ አማካሪ በመሆን እንዲሰራ ተመድበያለሁ፣የስራ መሪ ሳልሆን የስራ መሪነት ስራ የማልሰራ አመልካች እራሱ ከስልጣን አንስቶኝ የስራ መሪ ነው ማለቱ ክርክሩ መሰረተ ብስ ነው፤አመልካች የፌዴራል ተመዝጋቢ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ቢሆንም ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ክርክር በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 139(1) መሰረት የክልል ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፤የተጠሪ ስራ ውል ተቋርጧል የሚለው ክርክር ከተጀመረ በኋላ እንደ ማስረጃ የቀረበ እንጂ የደረሰኝ ነገር የለም፤ተጠሪ እስካሁን የድርጅቱ ስራ በመስራት ላይ እገኛለሁ፣ ከድርጅቱ እንዳልተሰናበትኩ እና በጅማ ከተማ እየሰራሁ እንዳለ በስር ፍ/ቤት በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ይርጋን በተመለከተ በCOVID 19 ወረሽን ምክንያት ፍ/ቤት ዝግ ስለነበረ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ትክክል በመሆኑ እንዲፀና በማለት ተከራክረዋል፡፡አመልካች አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራ ቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ጭብጥ አንጻር የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡መዝገቡን መርምረን እንደተገነዘብነዉ ተጠሪ የዳኘነት ጥያቄ ያልተከፈለ የ6ወር ደመወዝ እንዲከፈል እንዲወስንለት ሲሆን አመልካች በበኩሉ የስራ ዉል አስቀድሞ በህዳር 28 ቀን 2012ዓ.ም ላይ መቋረጡን እንዲሁም ተጠሪ ስራ ላይ እንዳልነበር በመግለጽ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግ መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡ይሁንና ማስረጃ የመመርመር እና ፍሬነገር የማረጋገጥ ስልጣን ያላቸዉ የስር ፍርድ ቤቶች የግራ ቀኙን ማስረጃ አመዛዝነዉ አመልካች ተጠሪን ከስራ ስለማሰናበቱ አለማስረዳቱን አረጋግጠዋል፡፡በተጨማሪ ተጠሪ ስራ ላይ አልነበረም የሚለዉ የአመልካች ክርክር ተቀባይነት ባለማግኘቱ ተጠሪ የጠየቀዉ የ6ወር ደመወዝ እንዲከፈል መወሰኑን ተገንዝበናል፡፡በእኛም በኩል በዚህ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመ መሆን አለመሆኑን በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉን ጭብጥ መሰረት በማድረግ መርምረናል፡፡

በሰበር አጣሪ ችሎት የተያዘዉ የመጀመሪያዉ ነጥብ አመልካች በፌዴራል መንግስት የተመዘገበ ድርጅት ከመሆኑ አንጻር በወረዳ ፍርድ ቤት መወሰኑ አግባብነት የሚመለከት ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤት ላይ አመልካች ይህንን ምክንያት በመግለጽ ጉዳዩ በወረዳ ፍርድ ቤት መታየት እንደሌለበት ያቀረበዉ ክርክር ስለመኖሩ መዝገቡ አያሣይም፡፡የሆነ ሆኖ ክርክሩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ የሚመለከት በመሆኑና ጉዳዩም የተወሰነዉ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 መሰረት ተደርጎ በመሆኑ ስራ ክርክር በክልል ፍርድ ቤቶች በወረዳ ፍርድ ቤት የሚታይ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 139 የተደነገገ ከመሆኑ አኳያ በወረዳ ፍርድ ቤት መታየቱ ስህተት ነዉ የሚባልበት ምክንያት የለም፡፡ሁለተኛዉ ነጥብ ተጠሪ ስራ አስክያጅ ነዉ እየተባለ መታለፉ ተገቢ መሆን አለመሆኑን የሚመለከት ነዉ፡፡ከዚህም አኳያ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ላይ እንደተመለከተዉ ተጠሪ ቀደም ሲል በስራ አስክያጅነት ሲሰራ እንደቆየ ነገር ግን ከሰኔ 1 ቀን 2011ዓ.ም ጀምሮ በአማካሪነት እንዲያገለግል መመደቡን ተጠሪ የተመደበበትን ደብዳቤ ጭምር በማቅረብ ያስረዳ መሆኑን፤ በአመልካች በኩልም ማስተባበያ ክርክር ያልቀረበበት እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ የአመልካች የደመወዝ ክፍያ ጥያቄ በስራ ክርክር ችሎት መታየቱ ስህተት ነዉ የሚያሰኝ ምክንያት የለም፡፡

ሌላዉ የአመልካች አቤቱታ ነጥብ ተጠሪ አስቀድሞ ከስራ ተሰናብቷል እናም ክሱ የ6 ወር ይርጋ ጊዜ አልፎበታል፤አልተሰናበተም ከተባለም ስራ ላይ አልነበረም የሚለዉ ክርክር በአግባቡ አልተመረመረም የሚል ነዉ፡፡በመሰረቱ አንድ ፍሬነገር መኖርን ወይም አለመኖርን በመግለጽ የተከራከረ ወገን ይህንኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ስ/ስህግ ቁጥር 258-259 እንዲሁም የፍ/ብ/ህግ አንቀጽ 2001 ድንጋጌ ይዘት ያስገነዝባል፡፡አመልካች ተጠሪን ህዳር 28 ቀን 2012ዓ.ም ከስራ ማሰናበቱ ገልጾ የተከራከረ ቢሆንም አመልካቹ ያቀረባቸዉ ማስረጃዎች በስር ፍርድ ቤት ተመዝኖ የስንብት ድብዳቤ ለተጠሪ አለመድረሱ ተረጋግጧል፡፡ከዚህም በተጨማሪ በተጠቀሱት ጊዜ ዉስጥ ተጠሪ ስራ ላይ ነበር ወይስ አልነበረም የሚለዉም የፍሬ ነገር ጉዳይ እንደመሆኑ የግራ ቀኙ ማስረጃ ተመዛዝኖ ተጠሪ ስራ ላይ እንደነበር በስር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ጉዳይ በመሆኑ ይህንን የፍሬነገር ድምዳሜ ይህ ሰበር ችሎት የማይቀበልበት ምክንያት የለም፡፡

እንደሚታወቀዉ ሰበር ችሎቱ የፍሬነገር ክርክር የማጣራት ፣ ማስረጃ የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን በህግ አልተሰጠዉም፡፡ይልቁንም የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለክት ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለዉ ትርጉም መሰጠቱ (አንቀጽ 2/4/ እና10 ይመለከታል) ስር መመልከቱ ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ የተዘረጋ ስርዓት መሆኑን የሚያሣይ ነዉ፡፡

በተለይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ

በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን፣የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ከፍ ሲል እንደተመለከተዉ ለሰበር አቤቱታዉ ምክንያት የሆነዉ የስራ ክርክር ጉዳይ ላይ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ ሲሆን አቤቱታዉ የቀረበዉም፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለበት ጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም (አንቀጽ 58 ይመለከቷል)፣ በቀን 02/09/2013 ዓ.ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሚኖረዉ ይሄዉ አዋጅ ነዉ፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ይዘት በአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

1ኛ/የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 374196 ላይ በቀን 05/08/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

3ኛ/በዚህ መዝገብ ላይ በ11/09/2013ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረዉ የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምሰት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ